# <u>የኢትዮጵያ ህልውና ዋስትና አለው - ሕዝቡ አንድነቱን እንደጠበቀ ነው!</u>

# የሁለት ሺህ ዘመን ፍፃሜ በድምቀት ተከብሮ ዋለ!

**ሐዋርያ ከቶሮንቶ፡- እንደ ምፅአት ቀን "ሊደርስ ነው" ሲባል የቆየው የኢትዮጵያችን የሁለት ሺህ ዘመናት ፍጻሜ እውነትም ኢትዮጵያውያን በያሉበት ደርሶባቸው የክት ልብሳቸውን እየለበሱ ወጥተው እየተቀበሉት ነው፡፡**

**ዛሬ መስከረም 8 ቀን 2007 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የኢትዮጵያ ሁለት ሺህ ዘመን መሸኛና የአዲሱ እንግዳ ዘመን መቀበያ ክብረ በዓል በቶሮንቶ ከተማ የተካሄደ ሲሆን፥ ቶሮንቶ ከተማ ድንገት ከማይታወቅ ዓለም በመጡ የከበሩ መንፈሳውያን ሕዝቦች የተወረረች አስመስሏት ውሏል፡፡ ከህጻናት እስከ አዛውንት "ወተት" የመሰለውንና በሀገራቸው ጥበብ የተዥጎረጎረውን ቀሚስና መላበሻ እየለበሱ ብቅ ብቅ ያሉት የኢትዮጵያ ልጆች፥ እንኳንስ ለባእድ ለእርስ በርስም ያስቀኑ ነበር፡፡ ይተዋወቁ የነበሩ ባልንጀራሞች በየግላቸው ዓለም ጠፍተው ቆይተው ዛሬን ጠብቀው ወደ አደባባዩ ብቅ በማለታቸው፥ በየእርምጃው ማይተቃቀፍ፥ ማይሳሳም፥ ከናፍቆቱ ብዛት እንደገና እየተሳሳመና እየተቃቀፈ ማይደሳሰስና የደስታ ሲቃ ማያሳይ አይታይም ነበር፡፡**




**ይህን በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ሕዝብ የተሳተፈበት ታሪካዊና ታላቅ በዓል ያዘጋጀው የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ሲሆን ቦታውም ክርስቲ መናፈሻ ብሉር ጎዳና ነው፡፡ ሥነሥርዓቱ የተዘጋጀው ከጥዋት እስከማታ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በመንደፍ**

ሲሆን ከመናፈሻው ጀርባ የሚያልፈው ታላቁ የብሉር ጎድና ከግራና ከቀኝ እስከ በዓሉ ፍጻሜ ለተሽከርካሪ ዝግ ሆኖ ውሏል፡፡



ዛሬ ልዩ ቀን ነበር፤ በዚህ የመናፈሻ ሜዳ ላይ፥ ኢትዮጵያውያን “ከ- እስክ” ሳይባሉ በዓዲሱ ዘመን አቀባበል ላይ ተገኝተዋል፡፡ ታላላቆቹ የሀገራችን ሃይማኖቶች በሜዳው ላይ የየግላቸውን ታላላቅ ድንኳኖች ተክለው ደስ ብሏቸው ሕዝቡን ሲያስተናግዱ ዋሉ፡፡ ጎረምሳ ወጣቶች በብዛት ሲታዩ፥ የእናት አባቶቻቸውን ባህርይ ወርሰው ሁሉም በጭዋነት በዓሉን አድምቀውት ውለዋል፡፡ በተለይ ህጻናትና ወጣቶች ከዛሬዋ እለት የሚገበዩት ትምህርትና የኢትዮጵያዊነት ኩራት ጥልቀት ያለው እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ተሳክቶለት ከዳር እስከ ዳር እየተዘዋወረ ለተመለከተ፥ በሁሉም አቅጣጫ ፍቅርና አንድነት የሞላበት የኢትዮጵያዊያኖች ቀን ነበር፡፡ ክፉ ነገር ካፉ እንዳይወጣ ሁሉም በየቤቱ ተማምሎ የመጣ ይመስል ነበር፡፡ ታዲያ ይህን ሳጤነው፥ ኢትዮጵያ እውነትም ለዘላለም ትኖራለች ብሎ እንዲደመድም ይገደዳል፡፡ ይህን ሪፖርት ለማዘጋጀት፥ ትኩረት ሰጥተን እንደተከታተልነው፥ ህብረትሰቡ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የተመሰቃቀለ ሁኔታ ግምት ውስጥ አስገብቶ ማንነቱን ለማስረዳት አደባባይ የወጣ ይመስላል፡፡ በየአጋጣሚው ያነጋገርናቸው ወገኖች፥ “ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ነን” በሚል የሲቃ ድምጽ መልእክታቸውን አስተላልፈውልናል፡፡ ”እንዴት ያምርብናል፥ እንዴት እንዋደዳለን፥ እስቲ እዩነ ...!” ይላሉ፡፡ “እኛን ሊጠብቅ ወጥቶ ፖሊስ ሥራ ፈትቶ ዋለ” እያሉም ይሳሳቃሉ፡፡ በነገራችን ላይ፥ ለበዓሉ ከተገኙት ባለሥልጣናት ሌላ ብዛት ያላቸው ሌሎች የካናዳ ህብረተሰብ ክፍሎችም ነበሩ፡፡




ሌላው መተዛዘቢያ ሆኖ የዋለው፥ ኢትዮጵያ ውስጥ ይደረጋል የተባለው የ“ሚለንየም” በዓል ዝግጅትና ተከትሎ የተከሰተው የኑሮ ውድነት ነው፡፡ “እንደዚህ በነጻና በድምቀት ሊከበር አይችልም፤ የአገር ውስጡ አልጫ ነው – በልጠናቸዋል” ይላሉ፡፡




የዛሬው በቶሮንቶ የተካሄደው የኢትዮጵያውያን በዓል በአካባቢው ሌላ ጥቅም ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል። ይህን የሕዝብ ቁጥርና ሥነሥርዓት የሚከታተል ማእከላዊ መንግሥትም ሆነ አካባቢያዊ ባለሥልጣናት ለኢትዮጵያዊው ማህበረሰብ ሊሰጡት የሚችሉትን ግምት ከፍ ሊያደርገው ይችላል። ምንም እኳን እስካሁንም በአፍሪካው ማህበርሰብ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ትልቁን ክብርና ሃላፊነት ሲወስዱ የቆዩ ቢሆንም፥ በዚህ መልክ ተሰባስበውና በማህበራቸው ዙሪያ ተሰልፈው መታየታቸው ግን ሊያስተጋባ የሚችለው መልእክት ቀላል እንደማይሆን ይገመታል።




ከዛሬ ጅምሮ ለሚቀጥሉት ቀናት፥ ተመሳሳይ ክብረ በዓሎች በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እያከበሩት ያለና ሊያከብሩት ዝግጅት ላይ ያሉ ሲሆን ውጤታቸውንም በንቃት የሚሳተፉና የሚከታተሉ ወገኖች ዘገባ እንደሚያቀርቡልን ተስፋ አለን።




ተተኪው አዲስ ዘመንና ዓመት የሰላምና የእድገት እንዲሆንልን በበኩላችን እየተመኘን፥ በሥልጣን ላይ ያሉት ክፍሎችም ሆኑ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ሁሉ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብና ፍላጎት ሊመረምሩ ይገባል እንላለን፡፡ በተግባር እየተስተዋለ ያለው ቁም ነገር፥ በአንድ በኩል ኢትዮጵያን ማጥፋት ከቶም አይቻልም የሚል መልእክት ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ በተቃዋሚነትና በማስመሰል ተሞሽሮ የነገ አምባገነን ለመሆን መሽቀዳደምም የተነወረ ልፋት መሆኑን ነው፡፡ ምርጫ የሌለው ትክክለኛው ምርጫ፥ የወሰደውን ቢወስድ ጸንቶ ለሕዝብ ሥልጣንና ለዴሞክራሲያው ሥርዓት መታገል ነው፤ ለዚህ በሃቅና በቆራጥነት ከታገሉ ሌላው ሁሉ ሊከተል ይችላል - ሥልጣንም ቢሆን፡፡ ሩጫውና መጠላለፉ ዓላማ የሌለው ሥልጣን ለመጨበጥ ከሆነ ግን፥ ሥልጣኑም የለ፤ ሃብቱም የለ - “ምንም የለ”!!፡


8. 9. 2007